# የMINNESOTA የሚከፈልበት ፈቃድ

ከጃንዋሪ 1፣ 2026 **ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል**

**የMinnesota የሚከፈልበት ፈቃድ ራስዎን ወይም ቤተሰብዎን ለመንከባከብ እረፍት በሚፈልጉበት ወቅት ክፍያዎችን እና የስራ ጥበቃዎችን ይሰጥዎታል።**

## ከሚከፈልበት ፈቃድ ምን መጠቀም እችላለሁ?

የህክምና ፈቃድ፡-

- ከእርግዝና፣ ከወሊድ እንዲሁም ከማገገም ጋር ተያያዥነት ያለውን እንክብካቤን ጨምሮ የራስዎን ከባድ የጤና ሁኔታ ለመንከባከብ

የቤተሰብ ፈቃድ፡-

- **የልጅ ክትትል ፈቃድ** – አዲስ ልጅን በመወለድ፣ በጉዲፈቻ ወይም በአሳዳጊ ምደባ በኩል ለመቀበልና ለመንከባከብ
- **የእንክብካቤ ፈቃድ** – ከባድ የጤና እክል ያለበትን የቤተሰብ አባል ለመንከባከብ
- **የወታደራዊ የቤተሰብ ፈቃድ** - ለንቁ ተግባር የተጠራውን የቤተሰብ አባል ለመደገፍ
- **የደህንነት ፈቃድ** – ከቤት ውስጥ ብጥብጥ፣ ወሲባዊ ጥቃት ወይም የራስዎ ወይም የቤተሰብ አባል መስጋት ጋር ለተያያዙ ጉዳዮች ምላሽ ለመስጠት

በአጠቃላይ፣ ሁኔታዎቹ ከሰባት ቀናት በላይ የሚቆዩና በጤና እንክብካቤ አቅራቢው ወይም በሌላ ባለሙያው የተረጋገጡ መሆን ይኖርባቸዋል።

## የሚከፈልበት ፈቃድ ሽፋን አለኝ?

በMinnesota ያሉ አብዛኛዎቹ ሰራተኞች በሚከፈልበት ፈቃድ የተሸፈኑ ናቸው። የአሰሪዎ መጠን ወይም እርስዎ የሚሰሩበት ሰዓት ወይም ቀናት ምንም ይሁን ምን እርስዎ ሽፋን አግኝተዋል። ገለልተኛ ስራ ተቋራጮች እና የግል ስራ ፈጣሪዎች በቀጥታ ሽፋን ባይሰጣቸውም መርጠው መግባት ግን ይችላሉ። ባለፈው ዓመት በMinnesota ውስጥ ለስራ አነስተኛ ክፍያ ከተከፈለዎት ለክፍያዎች ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ (በ2026 ለሚከፈልበት ፈቃድ የ$3,900 መነሻ)።

## ለምን ያህል ጊዜ ፈቃድ መውሰድ እችላለሁ?

በጥቅማ ጥቅም አመቱ እስከ 12 ሳምንታት የቤተሰብ ወይም የህክምና ፈቃድ ለመውሰድ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። በተመሳሳይ የጥቅማ ጥቅሞች አመት ውስጥ የቤተሰብና የህክምና ፈቃድ ካስፈለገዎት፣ በአጠቃላይ እስከ 20 ሳምንታት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

## ምን ያህል ይከፈለኛል?

የሚከፈልበትን ፈቃድ ሲጠቀሙ፣ ስቴቱ ክፍያዎችን ለእርስዎ ይፈፅማል። የሚከፈልበት ፈቃድ እስከ 90% የሚሆነውን ደመወዝዎን ይከፍላል፣ ይህም በገቢዎ ደረጃ ላይ በመመርኮዝ ከፍተኛው ሳምንታዊ መጠን በስቴቱ አማካኝ ሳምንታዊ ደመወዝ ላይ የተቀመጠ ነው። ይህ መጠን በየአመቱ የሚቀየሩ ሲሆን በ2026 የሚከፈልበት ፈቃድ መነሻ $1,423 ነው።

## ለሚከፈልበት ፈቃድ የሚከፍለው ማነው?

የሚከፈልበት ፈቃድ የሚሸፈነው ሰራተኞች እና አሰሪዎች በሚከፈሉት አረቦን ነው። የመጀመርያው አርቦን ተመን ከተሸፈነው ደመወዝ 0.88% ያህል ነው። የአረቦን ክፍልዎን ፈንድ ለማድረግ አሰሪዎ እስከ 0.44% ደመወዝዎን ሊቀንስ ይችላል።

## የእኔ ሥራ ቅጥር ጥበቃዎች ምንድን ናቸው?

- **የሥራ ጥበቃዎች፡-** በአጠቃላይ ከእረፍት ፈቃድዎ ሲመለሱ ወደ ሥራ ገበታዎ መመለስ ወይም ወደ ተመሳሳይ ቦታ መመለስ አለብዎት። የስራ ጥበቃዎች ከተቀጠሩበት ቀን ከ90 ቀናት በኋላ ተፈፃሚ ይሆናሉ።
- **የጤና መድን መቀጠል፡-** በአጠቃላይ ስንመለከተው እርስዎ በፈቃድ ላይ እያሉ አሰሪዎች የየራሳቸውን የጤና እንክብካቤ መድን አርቦ መዋጮ መቀጠል ይኖርባቸዋል።
- **ምንም የአጸፋ ምላሽ ወይም ጣልቃገብነት አይደረግም፡-** ለሚከፈልበት ፈቃድ ካመለከቱ ወይም ከተጠቀሙ አሰሪዎች ጣልቃ ሊገቡ ወይም በእርስዎ ላይ በአጸፋ ሊመልሱልዎት አይገባም። አሰሪዎች የእርስዎን የሚከፈልበት ፈቃድ ክፍያ መከልከል አይችሉም።

ከክፍያ ፈቃድ ጋር ለተያያዙ ጥያቄዎች፣ እባክዎ የMinnesota የሚከፈልበት ፈቃድን በ651-556-7777 ያነጋግሩ አሊያም ድረ-ገጻችንን ይጎብኙ።

አሰሪዎ የሥራ ቅጥር ጥበቃን እየጣሰ ነው ብለው ካሰቡ፣ በMinnesota የሰራተኛ እና ኢንዱስትሪ መምሪያ ያለውን የሰራተኛ ደረጃዎች ክፍል ያነጋግሩ።

**ተጨማሪ ይወቁ፡-** paidleave.mn.gov

ይህ መረጃ ለአካል ጉዳተኞች ወይም የቋንቋ እርዳታ ለሚፈልጉ ሰዎች ወደ የሚከፈልበት ፈቃድ አድራሻ በ 651-556-7777ወይም 844-556-0444 (ከክፍያ ነጻ መስመር) በመደወል በተለዋጭ ቅርፀት ሊሰጥ ይችላል።

MINNESOTA PAID LEAVE

Minnesota Paid Leave | 180 E 5th St Suite 1200 | Saint Paul, MN 55101

11/2025